የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራአምስተኛ ዓመት ቁጥር ፵፯
አዲስ አበባ ሐምሌ ፫ ቀን ፪ሺ፩ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

15th Year No. 47
ADDIS ABABA 10th July, 2009

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፮፻፵/፪ሺ፩ ዓ.ም

ከቱኒዚያ ሪፐብሊክ መንግሥት ጋር የተደረገ የአየር አገልግሎት ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ … ገጽ ፬ሺ፯፻፶

CONTENTS

**Proclamation No. 640/2009**

**Bilateral Air Transport Services Agreement** with the Government of the Republic of Tunisia Ratification Proclamation …….Page 4750

## አዋጅ ቁጥር ፮፻፵/፪ሺ፩

## በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በቱኒዚያ ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል የተደረገ የአየር አገልግሎት ስምምነትን ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

## PROCLAMATION NO. 640/2009

## A PROCLAMATION TO RATIFY THE AIR TRANSPORT SERVICES AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE GOVERNMENT OF THE REPUBLIC OF TUNISIA

የአየር አገልግሎት ለመጀመር የሚያስችል ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በቱኒዚያ ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል እ.ኤ.አ. ጃንዋሪ ፳፫ ቀን ፪ሺ፫ በቱኒስ የተፈረመ በመሆኑ፣

**WHEREAS,** a Bilateral Air Transport Services Agreement between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of Tunisia was signed in Tunis on 23rd day of January 2003;

ስምምነቱ በሥራ ላይ የሚውለው በሁለቱ ተዋዋይ ሀገሮች ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓት መሠረት ስምምነቱ መጽደቁን የሚያረጋግጡ የዲፕሎማቲክ ሰነዶች ልውውጥ ከሚደረግበት ዕለት ጀምሮ እንደሚሆን በስምምነቱ ውስጥ የተመለከተ በመሆኑ፣

**WHEREAS,** it is stipulated in the Agreement that the Agreement shall come into force on the date of the last notification of notes from either contracting parties confirming its ratification in accordance with its laws and regulations.

ስምምነቱን የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሰኔ ፲፰ቀን ፪ሺ፩ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያጸደቀው ስለሆነ፤

**WHEREAS,** the House of peoples' Representa-tives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Agreement at its session held on the 25th day of June, 2009;

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀፅ (፩) እና /፲፪/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia it is hereby proclaimed as follows:

## ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "ከቱኒዚያ ሪፐብሊክ መንግሥት ጋር የተደረገ የአየር አገልግሎት ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፮፻፵/፪ሺ፩" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## ፪. የስምምነቱ መፅደቅ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በቱኒዚያ ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል እ.ኤ.አ. ጃንዋሪ ፳፫ ቀን ፪ሺ፫ ቱኒስ ላይ የተፈረመው የአየር አገልግሎት ስምምነት በዚህ አዋጅ ፀድቋል።

## ፫. የትራንስፖርትና መገናኛ ሚኒስቴር ሥልጣን

የትራንስፖርትና መገናኛ ሚኒስቴር ስምምነቱ በሥራ ላይ እንዲውል የማድረግ ሥልጣን በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል።

## ፬. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ሐምሌ ፫ ቀን ፪ሺ፩ ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Bilateral Air Transport Services Agreement with the Government of the Republic of Tunisia Ratification Proclamation No. 640/2009".

## 2. Ratification of the Agreement

The Bilateral Air Transport Services Agreement signed in Tunis on the 23rd day of January 2003 between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of Tunisia, is hereby ratified

## 3. Power of the Ministry of Transport and Communications

The Ministry of Transport and Communications is here by empowered to undertake all acts necessary for the implementation of the Agreement.

## 4. Effective Date

This Proclamation shall enter into force up on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, this 10th day of July, 2009**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**